# ዜና ሠፅሐፌት

**በኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣንበሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ**
**በየ2 ወሩ የሚወጣ የውስጥ ጋዜጣ**

**ቅጽ 1 ቁጥር 61** **ኅዳር 2016 ዓ.ም**


የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

**ርዕይ**

በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ ማየት፤

**ተልዕኮ**

የግብርና ቴክኖሎጂን፣ አገልግሎቶችን፤ ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ መልካም ስም ያለውና፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓት በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኤኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት፤

**እሴቶች**

- ታማኝነት
- ሚስጥር ጠባቂነት
- ቁርጠኝነት
- የህግ የበላይነት
- ተጠያቂነት
- ለደንበኛና ተገልጋይ ትኩረት
- አለማዳላት
- አጋርነት
- ግልጽነት።
- ምላሽ ሰጪነት


**አድራሻ፡-**

**ፖ.ሳ.ቁ** 31303

**ስልክ ቁጥር** 0115534520

**የውስጥ መስመር** 227/234

**የፌስቡክ ገጻችን፡-** Ethiopian Agricultural Authority

**የቴሌግራም ገጻችን፡-** eaa_123

**ዌብሳይት፡-** www.eaa.gov.et


## የባለሥልጣኑን ሴት ሠራተኞችን ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ተገለጸ፤



የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን የሴቶች ማኅበራዊ ጉዳይ አካቶ ትግበራ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሴቶችን ብቃት በማሳደግና ወደ ተሻለ ደረጃ በማምጣት ለቁጥጥር ተግባሩ ያላቸውን ሚና በማጎልበት እና የማህበራዊ አካቶ ትግበራን በማሻሻል የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖን በመቀነስ የባለሥልጣኑን ሴት ሠራተኞችን ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ አስታወቀ።

ሁሉን አቀፍ የሴቶች ተሣትፎና ተጠቃሚነት ለማሳደግ የተጀመሩ ተግባራት ስኬታማ እንዲሆኑ የባለሥልጣኑ ሁሉም የሥራ ክፍሎች በያገባኛል ጉዳይ ሊሰሩ እንደሚገባ የገለጹት በሴቶች ማኅበራዊ ጉዳይ አካቶ ትግበራ ሥራ አስፈጻሚ ተወካይ አቶ ሰይድ ዑመር ተቋሙ አዲስ ቢሆንም ሴት አመራሮችን ጨምሮ ሁሉም የባለሥልጣኑ ሴት ሰራተኞችን የአቅም ክፍተት በመለየት ተከታታይ ስልጠናዎችን ለመስጠት እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ሰይድ አክለውም ሴቶች እራሳቸውን የሚያበቁበት የሴቶች ፎረም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ድጋፍ በማድረግና ለሴት ሰራተኞች ምቹ የስራ ከባቢ ለመፍጠር እና አቅማቸውን ለማጎልበት የሚያስችሉ ተግባራት በሥራ ክፍሉ እየተከናወኑ መሆኑንም ገልጸዋል።

የሴት ሠራተኞችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በሴቶች ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን ለማረቅ፣ በሥርዓተ ጾታ ምንነት እና ጾታዊ ትንኮሳን በመከላከል ዙሪያ ለሁሉም የተቋሙ ሰራተኞችና አመራሮች ግንዛቤ ለመፍጠር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየሰሩ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ሰይድ ሁሉም

የስራ ክፍሎች የሥርዓተ ጾታን ጉዳይ በእቅዳቸው አካተው የመስራት ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ ይሄን ተገንዝበው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡም ጠይቀዋል፡፡

አቶ ሰይድ አክለውም ለሴት ሰራተኞች ምቹ የስራ አካባቢ እንዲኖራቸው ከማድረግ አኳያ ከወሊድ ፈቃድ በኋላ ህፃናት ልጆቻቸውን የሚያቆዩበት የህፃናት ማቆያ ማዕከል በመሥሪያ ቤቱ በማቋቋም ህፃናቱ አስፈላጊውን እንክብካቤና ጥበቃ እንዲያገኙ እና ሴት ሰራተኞችም ህፃናት ልጆቻቸውን በቅርበት እንዲከታተሉ ለማስቻል በሥራ ክፍሉ ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ቢያቀርቡም እስከአሁን የሕጻናት ማቆያ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡ በዚህም ልጅ ያላቸው የመ/ቤቱ ሴት ሰራተኞች መቸገራቸውን ተናግረዋል፡፡

የሥራ ክፍሉ ውጤታማ ሥራ እንዲሰራ ከግብዓት፣ ከበጀት እና ከሕጻናት ማቆያ ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች ሊፈቱ እንደሚገባ የገለጹት አቶ ሰይድ የሴቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የአንድ ክፍል ብቻ ሳይሆን በተቋም ደረጃ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በባለሥልጣኑ ስትራቴጅክ እቅድና በሁሉም የሥራ ክፍሎች ዓመታዊ እቅድ ውስጥ በማካተት ሴቶችን አቅም ሊያጎለብቱ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

## .... ከገጽ 4 የዞረ!

በዚህም ለ 17 አዳዲስ ተቋማት እና ለ66 ነባር ተቋመት የብቃት ማተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡ አፈጻጸሙ በከፊተኛ ሁኔታ ሊጨምር የቻለው በፀረ ተባይ እና አፈር ማዳበሪያ ስራ አስፈፃሚ እንደ አዲስ ከተዋቀረ በኋላ ከዚህ በፊት ላለፉት 6 ዓመታት የብቃት ማረጋገጫ ሳያሳድሱ እገልግለግሎት ያገኙ የነበሩ ድርጅቶች እንዲያሳድሱ ጥብቅ ማሳሰቢያ በመተላለፉ እንደሆነ ዶ/ር በየነ አብራርተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፀረ ተባይና ማዳበሪያ ሬጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመን (ግልፅ ለማድረግ) እና ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎትን ለመስጠት እንዲሁም ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎች በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል የተለያዩ የሕግ ማዕቀፍ ስራዎች እንደተሰሩ ስራ አስፈፃሚው ገልፀው በተይም እነዚህ ስራዎች መስመር ይዘው እንዲሄዱና በተቀመጠላቸው ጊዜ እንዲከናወኑ የህግ ማዕቀፍ ስራዎችን ማሻሻል፣ ከክልል ተቆጣጣሪ አካላት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራት እንዲሁም ለባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት ትልቅ ሚና አላቸው ብለዋል፡፡

በመጨረሻም የፀረ-ተባይ ማዳበሪያ ሬጉላቶሪ ስራ ሰፊና አፅንኦት ተሰጥቶት ሊሰራ የሚገባ በመሆኑ ከዚህ በተሻለ መልኩ አፈፃፀማችንን ውጤታማ ለማድረግ ከሚመለከተው አካላት ጋር ያለንን ግንኙነት አጠናክረን እንሰራለን ብለዋል፡፡

PAGE 3

# የፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች በጀርሞች መላመድ  የሚያመጡትን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር መጎልበት ወሳኝ ነው ተባለ፤




የግብርና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ፣ ከአለም የጤና ድርጅትና የእንስሳት ጤና ድርጅት፣ ከአለም የምግብና የእርሻ ድርጅት እና ከዓለም አካባቢ ጥበቃ ድርጅት ጋር በመተባበር የፀረ-ተህዋሲያን መድሀኒቶች ሳምንት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ9ኛ ጊዜ በአገራችን ደግሞ ለ8ኛ ጊዜ ‹‹ የፀረ-ተህዋሲያን መድሀኒቶች በጀርሞች መላመድን በጋራ መከላከል›› በሚል መሪ ቃል ከህዳር 7- 14 /2016 ዓ.ም በተለያዩ ፕሮግራሞች ተከበረ።

የፀረ-ተህዋሲያን መድሀኒት በጀርሞች መላመድ በአሁኑ ስዓት በሰውና በእንስሳት ላይ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱንና ለዚህ ችግር መባባስ ምክንያት የሆነው  ህብረተሰቡ ስለመድሀኒት አወሳሰድ በቂ የሆነ ግንዛቤን ባለማግኘት ሲሆን፤  ያለ ጤና ባለሙያ የታዘዙ መድሀኒቶችን መውሰድ፣ የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ጉድለት፣ መልካም የሆነ የእንስሳት ጤና አጠባበቅ እና አያያዝ ልምድ ያለመኖር፣ የፀረ-ተህዋሲያን መድሀኒት ቅሪት ያለበትን ምግብ በመመገብ መሆኑን የገለፁት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእንስሳት መድሀኒት ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ሰለሞን ከበደ ጥቅም ላይ የዋሉ ፀረ-ተህዋሲያን መድሀኒቶች በቆሻሻ መልክ ወጥተው ጤናማ የተፈጥሮ አካባቢን ሲበክሉ፣ የጥራት ጉድለት ያለባቸው እና ህገ ወጥ ፀረ-ተህዋሲያን መድሀኒቶች ጥቅም ላይ ሲውሉና፣ የታዘዘን የፀረ-ተህዋሲያን መድሀኒት ማቋረጥ መጠኑን መጨመር ወይም መቀነስና  የመውሰጃ ስዓትን ማዛባት እንዲሁም  ከሌላ ሰው ተውሶ መውሰድ ችግሩን እንደሚያባብሱ አስረድተዋል።

የፀረ-ተህዋሲያን መድሀኒቶች በጀርሞች መላመድ የሚያስከትሉት አሉታዊ ተፅዕኖ ተጓዳኝ ጠንቃቸው ከፍ ሲል የማዳን ኋይላቸው ዝቅ ያለ ሌሎች ውድ መድሀኒቶችን ለመጠቀም ወይም አንዳንዴም ምንም አይነት አማራጭ እንዳይኖር ሊያደርግ እንደሚችል የገለፁት ዶ/ር ሰለሞን ከሰው ወደ እንስሳት ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎች የስርጪት መጠን በመጨመር እንዲሁም ምርታማነትን በመቀነስ በአገር ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ላይ የከፋ ጉዳት እንደሚያደርስ ተናግረዋል።

የፀረ ተህዋሲያን መድሀኒትን ውጤታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የእያንዳንዱ መንግስታዊይም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ባለሙያዎች እንዲሁም መላው ህብረተሰብ በቅንጅት ሆነው መስራት ያስፈልጋል ያሉት ዶ/ ር ሰለሞን  በተለይም የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት መንግስት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አተኩሮ ሊሰራ እንደሚገባ አብራርተዋል።

PAGE 4

# ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የፀረ-ተባይ ማዳበሪያ ቁጥጥር ስርዓት ተደራሽነትን ለማስፋት በትኩረት እየተሰራ መሆኑ ተገለፀ፡፡



የፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ሪጉላቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር በየነ ልደቱ ጥራታቸው፣ ደህነታቸውና ፍቱንነታቸው የተረጋገጠ የፀረ-ተባይና ማደበሪያዎች በሚፈለገው ደረጃ ተደረራሽነታቸውን ለማስፋት ባለስልጣኑ በሚኒስትሮች ምክርቤት በደንብ ቁጥር 509 የተሰጠውን ስልጣንና ተገባር በአግባቡ ለመፈጸም የሚያስችል አዲስ መዋቅር ተግባራዊ አድርጎ ወደ ስራ መግባቱን አስረድተው ፡፡ ይሄንኑ መሰረት ባደረገ መልኩ ከቀድሞ የዕፅዋት ጤናና ጥራት ዳይሬክቶሬት በመነጠል እንደተደራጀና የ2016 በጀት ዓመት እቅድ በማዘጋጀት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

በዚህም በሩብ ዓመቱ ለ30 የፀረ ተባይ እና ማዳበሪያ ናሙናዎች ሙከራ ምርምር ፈቃድ (trial authorization) ለመስጠት ታቅዶ 29 መሰጠቱን በሌላ በኩል 60 የፀረ ተባይ እና ማዳበሪያ መስፍርቶቹን ያሟሉ ዶዜየሮችን ለመረከብ ታቅዶ 72 እንደተፈፀመና ከዕቅዱ በላይ ሊጨምር የቻለው አገልግሎቱ ለተወሰነ ጊዜ ተቋርጦ በመቆየቱ በሩብ ዓመቱ ይቀርባል ተብሎ ከታቀደው በላይ ዶዜየሮች በመቅረባቸው መሆኑን ስራ አስፈፃሚው አብራርተዋል፡፡ ዶ/ር በየነ አያይዘውም ለ600 ፀረ ተባይ እና አፈር ማዳበሪያዎች የቅድመ የማስገቢያ ፈቃድ መስጠት ታቅዶ ለ 582 የፀረ ተባይ እና አፈር ማዳበሪያዎች ወደ አገር የማስገቢያ መስፈር ማሟላታቸው ተረጋግጦ የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ እንደተሰጣቸው፤ለ10000 ቶን ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የፀረ-ተባይና ማዳበሪያዎች ላይ ኢንስፔክሽን በማከናወን ጥራትን ለማረጋገጥ ታቅዶ በ15181 ቶን የፀረ ተባይ /ማዳበሪያዎች ላይ የኢንስፔክሽን ስራ መከናወኑን በተመሳሳይ ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ፀረ-ተባይና ማዳበሪያ ጭነቶች መስፈርቶች ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ለ500 ጭነቶች የጉምሩክ ማስለቀቂያ ደብዳቤ መስጠት የታቀደ ሲሆን ለ445 ጭነቶች አገልግሎቱን መስጠት ተችሎዋል ብለዋል፡፡

በሩብ ዓመቱ በፀረ ተባይ እና አፈር ማዳበሪያ ስራ ላይ የተሰማሩ የሀገር ውስጥ አምራቾች፣አስመጪዎች፣ ጅምላ አከፋፋዮች እና የክምችት ማዕከላት እና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ ደህንነታቸው እና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ለአዲስ 5 ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት እና ለ10 ነባር ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለማደስ በእቅድ የተይዘ ነበረ፡፡

**ወደ ገጽ 2 ይዞራል……!**

# ለባለሥልጣኑ ርዕይ፣ ተልዕኮና ዓላማ ከግብ መድረስ እንቅፋት የሚሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና ብልሹ አሰራሮችን መታገል ለአንድ አካል ብቻ የሚተው አይደለም!

አቶ አበበ ገለታ የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ



ኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን በግብርና ዘርፉ የተጠናከረ ሬጉላቶሪ ሥርዓት በመዘርጋትና በመተግበር በዓለም አቀፍ እና በአገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ በሰው፣ በእንስሳትና በእጽዋት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ላይ ጎጂ ተጽዕኖ እንዲቀንስ ወይም እንዲወገድ የማስቻል ዓላማ ይዞ የፌዴራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 45 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት የተቋቋመ የፌደራል መ/ቤት ነው፡፡ ይሄን የተቋቋማለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያለውን ግብዓት በአግባቡ መጠቀም፣ ብቁ የሰው ኃይል መገንባት፣ የተመደበለት ፋይናንስ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን መቆጣጠር፣ ተቋማዊ ሪፎርም መገንባት፣ ከእቅድ ጀምሮ እስከሪፖርት ድረስ ሁሉም ሠራተኛ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግና የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና ብልሹ አሰራሮችን መቀነስ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ ወር የዜና መጽሔት እትማችን እነዚህን ስራዎች በዋናነት ከማያስተባብሩት የባለሥልጣኑ የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከሆኑት አቶ አበበ ገለታ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡ መልካም ንባብ!

ሕዝብ ግንኙነት፡- የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ በዋናነት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት ምንድን ናቸው?

አቶ አበበ፡- የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሆኖ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ነው የሚያከናውነው፡፡ ለአብነት ለመጥቀስ ያክልም የባለስልጣን መስሪያ ቤቱን የሰው ኃይል አስተዳደር ክፍልን እቅድ እንዲያዘጋጁ ከማድረግ ጀምሮ ይከታተላል፤ ይመራል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ሰርኩላሮችና አግባብነት ያላቸው መመሪያዎችን ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል፡፡ እንዲሁም የባለሥልጣኑ ስትራቴጅካዊና ዓመታዊ እቅድ እንዲዘጋጅና እንዲተገበር በበላይነት የመከታተል፤ መ/ቤቱ በህግ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የሚሰበሰቡ ገቢዎች በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ወደ ባንክ መተላለፋቸውን መቆጣጠር፤ የተቋሙን ሐብትና ንብረት፣ የሎጅስቲክና ግብዓት አያያዝና አጠቃቀም የመንግስት ሕግንና ደንብን በተከተለ አግባብ ስለመተግበሩ መከታተል፣ የተቋሙን የግዥ አፈጻጸም ከእቅድ ጀምሮ የተገዙ የተቋም ንብረቶችና ግብዓቶች ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እስከሚሰራጩ ድረስ ክትትል በማድረግ መምራት፣ የተቋሙ ቋሚ ንብረቶች አያያዝና አጠቃቀም ዘመናዊ አሰራርን የተከተሉ እንዲሆኑ በበላይነት መከታተል፣ የመ/ቤቱን የትራንስፖርት አገልግሎት የሚያሳልጡ አሰራሮች እንዲዘረጉና እንዲዳብሩ ያደርጋል፡፡

....... ከገጽ 5 የዞረ!

በተጨማሪም የባለሥልጣኑን የአይሲቲ የብልጽግና ልማት እንዲተገበርና ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሲስተሞች እንዲዘረጉ የማስተባበር፣ ከተገልጋዩ ሕብረተሰብ የሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች በፍጥነት ተገቢ ምላሽ የሚያገኙበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ የመናድረግና የመከታተል ተግባራትንም ያከናውናል፡፡ በአጠቃላይ የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ በ6ቱ የሥራ ክፍሎች ማለትም ሰው ኃብት፣ መሰረታዊ አገልግሎት፣ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን፣ ግዥና ፋይናንስ፣ ለውጥና ስትራቴጅክ ሥራ አስፈጻሚዎች ውስጥ የሚከናወኑ ሥራዎችን በሙሉ ያስተባብራል፤ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤ ያስተገብራል፡፡

**ሕዝብ ግንኙነት፡-** ባለሥልጣኑ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚያስችለው የበቃ የሰው ኃይል ከመፍጠር አኳያ ምን የታሰበ ነገር አለ?

**አቶ አበበ፡-** በአመለካከትና በክህሎት የበቃና የጠራ ግንዛቤ ያለው የሰው ኃይል መኖር ለተቋም ስኬት እጅግ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ ይሄን ከግምት ውስጥ በማስገባት የባለሥልጣን መ/ቤታች የሰው ኃይል ልማት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው፡፡ ለዚህም ተቋሙ የሠው ኃብትና ብቃት ሥራ አመራር በኩል በየክፍሉ ያሉ የአጭርና የረጅም ጊዜ ሥልጠና ፍላጎቶች ተለይተው እንዲታቀዱና እቅዱን መሠረት በማድረግም በብቃት፣ በክህሎትና በእውቀት ያሉ ክፍተቶችን በመለየት ክፍተቱን የሚሞሉ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ በማድረግ ለተቋሙ ግብ መሳካት የሚተጋ ብቃት ያለው የሰው ሀይል እንዲኖር ለማድረግ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በዚህም የየክፍሉ የሥልጠና ፍላጎቶች ተለይተውና ተደራጅተው ያለቁ ሲሆን በቅርቡም ለተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች የሚቀርብ ይሆናል፡፡ አሁን ላይም ለረጅም ጊዜ የትምህርት እድል ሠራተኞች በውድድር ላይ ይገኛሉ፤

በሌላ በኩል ከሥልጠና በዘለለ የሠራተኞችን አቅም ለመገንባት የሥራ ክፍሎች ከሌሎች አቻ መ/ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረጉበትን ሥርዓት እየዘረጋን ነው፤ በቅርቡም የባለሥልጣኑ ተቋማዊ የአመራር ለውጥ ደብረዘይትና ሰበታ በመሄድ ከሌሎች አቻ መ/ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ ያደረገ ሲሆን ያደረገውን የልምድ ልውውጥ በመቀመር በተቋማችን ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ ነው፤ ይሄ በሌሎች ክፍሎችም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

**ሕዝብ ግንኙነት፡-** በባለሥልጣኑ የሥራና የበጀት እቅድና ሪፖርት ላይ ሁሉም ሠራተኛ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖረው ብሎም ሁሉም የሥራ ክፍሎች በጀታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙና ውጤታማ ሥራዎችን እንዲሰሩ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን ቢያብራሩልን?

**አቶ አበበ፡-** ይሄን ጥያቄ በሁለት ከፍዬ ለመመለስ እሞክራለሁ፡፡ የመጀመሪያው በባለሥልጣኑ ስትራቴጅክ እቅድ በተያያዘ ነው፡፡ ሁሉም ሠራተኛና አመራር ከእቅድ ጀምሮ ባለሥልጣኑ በሚተገብራቸው ስትራቴጅዎችና ፕሮግራሞች ዙሪያ የጋራ አረዳድ ይዞ ለተቋሙ ግብ መሳካት እንዲሰራ ለማድረግ አሳታፊነት መኖር አለበት በሚል በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ነው፡፡ በሁሉም የሥራ ክፍል የሚታቀዱ እቅዶች ሠራተኞች ጭምር የተሳተፉበትና የጋራ መግባብት የተደረሰበት እንዲሆንና አፈጻጸሙም በየጊዜው የጋራ እየተደረገ መሄድ እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጦ በዚያ መልኩ እየተተገበረ ነው፡፡

PAGE 7

በቅርቡም ለቡድን መሪ እና ለሥራ ኃላፊዎች በቅርቡ በአዳማ በሊደርሽፕ፣ በቲም ቢዩልዲንግና በተቋሙ ስትራቴጅክ እቅድ ዙሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል። ይሄ ሥልጠና እስከታችኛው ፈጻሚ ሠራተኛ ድረስ ለመስጠትም በእቅድ ተይዞ እየተሰራበት ይገኛል። ሁለተኛው የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ መሪ ሥራ አሥፈጻሚዎች በጀት ለእያንዳንዱ ሥራ ክፍል ተመድቦ በፋይናንስ የአሠራር ሥርዓት መሰረት የየክፍላቸውን በጀት እየተጠቀሙ ነው። የድጋፍ ሠጪ ክፍሎች በጀት በፑል ወይም በጋራ የተቀመጠ በጀት ስለሆነ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የበጀት እቅዱን እንዲያቀርብ ተደርጎ ሥራዎችን ለመሥራት ሲፈልግም ፕሮፖዛል እየሰራ አቅርቦ እያስፈቀደ በዚያ መንገድ በጀቱን በፍትኃዊነት እንዲጠቀሙ እየተደረገ ነው። ነገር ግን በጀቱ የጋራ ስለሆነ የበጀት አጠቃቀሙ እንደየሥራ ክፍሉ እንቅስቃሴ ይወሰናል ማለት ነው።

**ሕዝብ ግንኙነት፡-** ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሕግ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት የሚሰበስበው ገንዘብ በአግባቡ እየሰበሰበ መሆኑንና ወደ ባንክ መተላለፋቸውን በምን አግባብ ክትትል እየተደረገ ነው?

**አቶ አበበ፡-** የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን በህግ ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት መካከል አንዱ ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ የአገልግሎት ገቢ ገንዘብ መሰብሰብ ይገኝበታል። የሥራ አመራር ዋና አስፈጻሚም መ/ቤቱ በህግ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የሚሰበሰቡ ገቢዎች በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ወደ ባንክ መተላለፋቸውን ይከታተላል። ይሄን የሚከታተልበት አግባብም በባለሥልጣኑ የሚሰበሰቡ ገንዘቦችን በሚመለከት በሲቪል ሰርቪስ መደብ ተቀርጾለት ባለሙያም ተመድቦለት ወደ ሥራ የገባ በመሆኑ ይሄ ባለሙያ ዋና ሥራው ገቢዎችን መሰብሰብና ለዚህ በተከፈተው አካውንት ገቢ ማድረግ ነው። ሥለዚህ የሥራ አመራር ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከባለሙያው የሚመጣውን ሪፖርትና የባንክ ሰነድ በመመልከት ክትትል ያደርጋል። ለምሳሌ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከገቢና ወጪ የገብርና ምረትቶች አንድ መቶ ሃምሳ አራት ሽህ አንድ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር (154199 ብር) ፣ ከዘር ጥራት ቁጥጥር አገልግሎት ክፍያ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ብር (6800 ብር) በአጠቃላይ አንድ መቶ ስልሳ አንድ ሽህ ብር (161000 ብር) ገቢ ተደርጓል።

**ሕዝብ ግንኙነት፡-** የባለሥልጣን መ/ቤቱ ሀብትና ንብረት እና የሎጀስቲክና የግብዓት አጠቃቀም ሕግንና ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን ምን እየተሰራ ነው?

**አቶ አበበ፡-** ተቋሙ የተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ ኃብትና ንብረቱን ሕግና ሥርዓት በተከተለ መንገድ በአግባቡ መጠቀም አለበት። እንደ ሥራ አመራር ሥራ አስፈጻሚ ተቋሙ ያለው ኃብት ውስን ስለሆነ ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ ሁሉም በፍትኃዊነት እንዲጠቀም ጠንካራ እርምጃዎች መወሰድ አለበት በሚል እዚህ አካባቢ በርካታ እርምጃዎችን እየወሰድን ነው። ለአብነትም ከሠው ኃብት አንድ እና ከጠቅላላ አገልግሎት ሁለት በአጠቃላይ ሶስት አባላት ያሉት ኮሚቴ በማዋቀር ተቋሙ ያለውን ውስን ንብረት በአግባቡ እና በፍትኃዊነት ለመጠቀም ትርፍ ንብረቶች ያሉባቸውን የሥራ ክፍሎች በመለዬት ከየክፍሎቹ ንብረቶቹን የማሰባሰብና እጥረት ላለባቸው ክፍሎች የማሰራጨት ሥራ ተሰርቷል። በዚህም አንድ ቦታ ተከማችተው የነበሩ ኮምፒውተር፣ ጠረጴዛ የመሳሰሉ



ግብዓቶችን በፍትኃዊነት ማከፋፈል ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የግብርና ሚ/ር ሚኒስትር ክቡር ዶ/ር ግርማ አመንቲ ተቋማችንን ሊጎበኙ በመጡበት ወቅት ተቋሙ አዲስና ሥራውም እጅግ ሰፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደመ/ቤት ያሉብንን የግብዓትና የሎጅስቲክ ችግሮችን አንስተንላቸው የነበረ በመሆኑ በእነሱ በኩል ድጋፍ ለማድረግና ተቋሙን በግብዓት ለማጠናከር የሚያስችል አውንታዊ ምላሽ አግኝተናል፤ እሱንም በመጠባበቅ ላይ ነን፡፡

**ሕዝብ ግንኙነት፡-** ከግዥ መዳተትና ከትራንስፖርት ስምሪት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን በዘላቂነት ለመፍታት ምን እየተከናወነ ነው?

**አቶ አበበ፡-** ከግዥ ጋር በተያያዘ መዳተት አለ የሚለው ቅሬታ ተገቢ ነው፡፡ ነገር ግን አጠቃላይ የመንግስት ግዥዎች በመንግስት ግዥ ኤጀንሲ በማዕቀፍ የሚገዙ በመሆናቸው ከዚያ ጋር ተያይዞ የተከሰተ ነው፡፡ ሆኖም በእኛ ደረጃ የሚገዙ ጥቃቅን ግዥዎች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲገዙና እንዲሰራጩ ለማድረግ የባለሙያዎችን አቅም ለማሻሻል የሚያስችሉ የተለያዩ ሥልጠናዎችን እንዲያገኙ አድርገናል፡፡ ለአብነትም በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 13 አካባቢ ባለሙያዎች በግዥ አፈጻጸም ዙሪያ ስልጠና አግኝተዋል፡፡

ሥለሆነም ሕግና መመሪያው በሚፈቅድልን መሰረት በእኛ ደረጃ የሚፈጸሙ ግዥዎች በተመደበልን በጀት መሰረት ተገዝተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ትኩረት ሰጥተን እየሰራን ነው፡፡

ከትራንስፖርት ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮች ምንጫቸው ሁለት ነው ብለን እንወስዳለን፡፡ አንደኛው ባለሥልጣኑ ካለው የትራንስፖርት እጥረት የሚነሳ ሲሆን ይሄን ለመፍታት የተቋሙ የበላይ የሥራ ኃላፊዎች ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከግብርና ሚ/ርና ከሌሎች መንግስታዊ ተቋማት እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር እየተነጋገርን ነው፡፡ ሌላኛው ያለውን ትራንስፖርት ፍትኃዊ በሆነ መንገድ ካለመጠቀምና ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ቅሬታ ነው፡፡ ይሄን ችግር ለመፍታት ከአሁን በፊት ትራንስፖርት አካባቢ ሥራዎች በአንድ ሰው ብቻ ይሰሩ የነበረ ሲሆን አሁን ላይ የሥራ ክፍፍል እንዲኖር ተደርጓል፡፡ በዚህም ሥምሪት የሚወጡ መኪኖችን ተራ የሚያሲዝና የሚቆጣጠር አንድ ባለሙያ፣ ሥምሪት የሚሰጥ አንድ ባለሙያ እና ሥምሪት የሚወጡ መኪኖችን የነዳጅ አጠቃቀማቸውን የሚቆጣጠር አንድ ሌላ ባለሙያ ተመድበው ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡ ይሄ ብቻ ሳይሆን መኪኖቻችን ወደ ጋራዥ በሚገቡበት ጊዜ በታዘዘው መሰረት ተሰርተው መውጣታቸውን የሚቆጣጠር ባለሙያም የተመደበ ሲሆን የመኪኖችን የነዳጅ አጠቃቀምና የጋራዥ ሂደታቸውን በተመለከተ የሚቆጣጠር 3 አባላት ያሉት የባለሙያዎች ቡድንን በኮሚቴ መልክ በማቋቋም እየሰራን ነው፡፡ በቀጣይም ሌሎች እርምጃዎችን ለመውሰድና ጠንካራ ሥርዓት ለመዘርጋት ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር ተቀናጅተን የምንሰራ ይሆናል፡፡

**ሕዝብ ግንኙነት፡-** እርስዎ በሚከታተሏቸው የሥራ ክፍሎች በርካታ ብልሹ አሰራሮችና የመልካም አስተዳደር ችግሮች

የሚያስከትሉ ድርጊቶች እንደሚፈጸሙ ይነገራልና እነዚህን ችግሮች በተመለከተ ጥቆማዎችን በምን መልኩ እየተቀበላችሁና ችግሩን በዘላቂነት ለመቅረፍ ምን እየተሰራ እንደሆነ ቢያብራሩልን?

**አቶ አበበ፦** ባለሥለጣኑ የተጣለበትን አገራዊ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የመልካም አስተዳደር ችግሮችና ብልሹ አሰራሮችን በተመለከተ ጠንካራ ሥርዓት መዘርጋትና አስተማሪ እርምጃዎችን መውሰድ ለነገ የሚባል አይደለም። እኛም እንደተቋም ከአሁን ቀደም ከሕግና ከመመሪያ ውጭ ይፈጸሙ የነበሩ አንዳንድ የተለመዱ አሰራሮች እንዲቆሙና በሕግና በሥርዓት ብቻ እንዲመሩ ለማድረግ እየሰራን ነው። የተለመደን ብልሹ አሰራር ለማስቆም በምናደርገው ጥረት ቻሌንጆች ቢኖሩም ያለው ብቸኛ አማራጭ አሰራሮች ሁሉ ሕግና ሥርዓትን የተከተሉ እንዲሆኑ ማድረግ ብቻ መሆኑን በእምነት ይዘን እየሰራን ነው። በተጨማሪም ከባለሥልጣኑ ተቋማዊ የለውጥ አመራር ጋር በመሆን ጥቆማዎችና ቅሬታዎች የሚቀርቡባቸውን የኃሳብ መስጫ ሳጥኖች አስቀምጠናል፤ በእነዚህ የአስተያየት መስጫ ሳጥን የሚቀርቡ ቅሬታዎች በየጊዜው እየተፈቱ እንዲሄዱ እናደርጋለን። በተጨማሪም የአገልግሎት አሰጣጣችን ከቅሬታና ከብልሹ አሰራር የጸዳ እንዲሆን በየጊዜው ለሠራተኞች ግንዛቤ ለመፍጠር በእቅድ ይዘን እየሰራንበት ነው። በመሆኑም ከመልካም አስተዳደር መጓደልና ከብልሹ አሰራር ጋር በተያያዘ ተጨባጭ መረጃዎች በጥቆማ መልክ ከማንኛውም አካል ቢመጡ አስተማሪ እርምጃ የምንወስድ ይሆናል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ግን ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርኩት አንዳንድ ከሕግና ከመመሪያ ውጭ የሆኑ ጥያቄዎችን ይዘው መጥተው ጥያቄው ሕግና አሰራርን የተከተለ አይደለም በሚል ውድቅ ሲደረግባቸው ችግሮች አሉ በሚል የሚነገረው ንግግር ትክክል አይደለም። ሁሉም አካል ልብ ሊለው የሚገባ ጉዳይ ጥያቄዬ ከሕግና ከመመሪያ ውጭ አይደለም ወይ የሚለውን ደጋግሞ እንዲያስብና ሕጋዊ ያልሆኑ አሰራሮችን መከተል እንደሌለበት በዚህ አጋጣሚ መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ። ከሕግ፣ ከመመሪያና ከአሰራር ውጭ ዛሬም ወደፊትም አናስተናግድም የሚለው ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በቀጣይም የመልካም አስተዳደር ችግሮችና ብልሹ አሰራሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍ ከ4 የባለሥልጣኑ የሥራ ክፍሎች ጋር ማለትም ከሕግ፣ ከኦዲት፣ ከሥነ ምግባር መከታትያና ከተቋማዊ ለውጥ ጋር ተቀናጅቶ ለመሥራት አቅጣጫ ተቀምጦ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እየሰራን እንገኛለን።

**ሕዝብ ግንኙነት፦** ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት

**አቶ አበበ፦** ሥራዎች ሲሰሩ ከችግር ነጻ በሆነ መንገድ አይደለም። በሳለፍነው የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ሥራዎችን ሥንሰራ ያጋጠሙ ችግሮች በርካታ ናቸው። በዋናነት ግን ተቋሙ አዲስና በሽግግር ላይ ያለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የግብዓት (ማለትም የኮምፒውተር፣ ወንበርና ጠረጴዛ፣ ተሽከርካሪ) እጥረት፤ የበጀት፣ የሰው ኃይል እጥረት፤ የሕጻናት ማቆያና የጥበቃዎች ማረፊያ አለመኖር የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚመለከተን አካላት ተቀናጅተንና ተናበን እንድንሰራ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። በተጨማሪም የተቋማችን ርዕይ፣ ተልዕኮና እቅድ ከግብ ለማድረስ ለእድገታችን እንቅፋት የሚሆኑ የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና ብልሹ አሰራሮችን መታገል ለአንድ አካል ተለይቶ የሚተው ባለመሆኑ ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበት ለማሳሰብ እወዳለሁ።

# ቡፌ አምድ

## ለጠቅላላ እውቀት

⇒የአለማችን ትልቋ ሀገር ሩስያ ስትሆን 17.09 ሚሊየን km2 የሆነ የቆዳ ስፋት አላት::

⇒በአለማችን ላይ በርሀማዋ ሀገር ሊቢያ ስትሆን ከአጠቃላይ የቆዳ ስፋቷ 99% የሚሆነው በረሀማነት የሚፈረጅ ነው::

⇒በአለማችን ላይ ምንም አይነት ወንዝ የሌላት ሀገር ሳውድ አረቢያ ነች::

⇒ጊንጥ ከ 6-12 ወራት ምግብ ሣትመገብ መቆየት የምትችል እንስሳ ነች።

⇒ቀን እና ለሊት እኩል የሚሆኑት ፀሐይ የምድር ወገብ ወይም equator ላይ ስትሆን ነው።

⇒ጅብ የሚስቀው ለጓደኞቹ ምግብ ማግኘቱን ሲናገር ነው።

⇒የታይታኒክ መርከብ የሰጠመችው ከእንግሊዝ ሣውዝሃምፕተን ወደ አሜሪካ ኒውዮርክ ስትጓዝ ነው።

## ሥለእኛ



የአለማችን ረጅሙ የከንፈር ሳህን ሪከርድ ባለቤት ኢትዮጵያዊቷ አታዬ ኢሊጊዳኜ ነች። በደቡብ ኢትዮጵያ የሱርማ ተወላጅ የሆነችው አታዬ እኤአ በ2014 19.5 ሳ.ሜ ርዝመት ያለውን የከንፈር ሳህን በማንጠልጠል ሪከርዱን ይዛለች:: በዚህም በራሷ ቀደም ሲል በ15 ሳ.ሜ ተይዞ የነበረውን ሪከርድ ሰብራለች:: በሱርማ ጎሳ ከንፈርን መለጠጥ ከጋብቻ አንድ አመት በፊት የሚከናወን ተግባር እንደሆነና ጥሎሹም በርዝመቱ ልክ እንደሚሆን ይነገራል:: ሳህኑ በሱርማዎች ጥበብ ለዚህ በሚሆን አፈር የሚዘጋጅ ነው።

## ውድቀትን እንደውዳቂነት አትቁጠር!

*****

ታዋቂው የአመራር ሊቅ ጃን ማክስዌል “Failing Forward” በተሰኘው ዝነኛ መጽሐፉ ውስጥ፣ “ከወደክ፣ ውዳቂ ነህ ማለት ነው?” የሚልን ምእራፍ ጽፏል። ይህንን ምእራፍ የሚጀምረው፣ “ውድቀት ልብን ካልጎዳ ችግር የለበትም፣ ስኬት ደግሞ ጭንቅላት ላይ እስካልወጣ ድረስ ጥሩ ነገር ነው” የሚለው የግራንት (Grantland Rice) አባባል በመጥቀስ ነው። ከዚያም የሚከተሉትን ታዋቂና ስኬታማ ሰዎች ልምምድ ለምሳሌነት አስፍሯል። በሙዚቃ እውቀቱ በአለም ታዋቂ የሆነው Wolfgang Mozart በዘመኑ በነበረ ገዢ በፈርዲናንድ፣ “ዜማህ ብዙ ይጮሃል፣ ብዙ ቃላትም ታበዛለህ” የሚልን ተስፋ አስቆራጭ መልእክት የሰማ ሰው ነበር። በዓለም የታወቀውና በአንድ ስእል ሽያጭ በአለም ከፍተኛ ገቢ ያስገኘው ሰአሊ Vincent Van Gogh በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አንዲትን ስእል ብቻ ነው የሸጠው። በፈጠራ ግኝቱ በአለም ታዋቂ የሆነው Thomas Edison በልጅነቱ፣ “ትምህርት የማይገባው” ተብሎ ነበር። የታወቀው ፈላስፋና አዋቂ Albert Eintsein ከአስተማሪ የሰማው ተስፋ አስቆራጭ ቃል፣ “ለምንም ጥቅም የማትውል ሰው ነህ” የሚል ነበር። እነዚህን ሰዎች ከነበሩት ሁኔታ አልፈው ወደስኬት ጎዳና እንዲገቡ ያደረጋቸው የጋራ ባህሪይ፣ ውድቀትን እንደውዳቂነት አለመቁጠር ነው።  አንድ ግብ ጋር ለመድረስ መስራት፣ መንቀሳቀስና አዳዲስ ነገሮችን መጀመር እንዳለብኝ በማወቅ ወደፊት መገስገስ የስኬት ዋነኛው መንገድ ነው። ጉዞ ካለ እንቅፋት አለ፤ ሙከራ ካለ አለመሳካት አለ፤ ንግድ ካለ ክስረት አለ … ስሌቱ ይኸው ነው።  በተቃራኒው ምንም አይነት ስህተትና አለመሳካት እንዳይደርስብኝ ከፈለግኩኝ ቀላሉና ብቸኛው መንገድ አለመንቀሳቀስ ነው። አንዳንድ ሰዎች መውደቅ እንዳይከተል ሲሉ ምንም ነገር አለመሞከርን ይመርጣሉ - ሌላ የከፋ ስህተትና ውድቀት!  ስህተትንና ውድቀትን በጥብቅ የሚፈሩ ሰዎች አንድ ወይም ሁለት ጊዜ  ስለወደቁ ብቻ ውዳቂ እንደሆኑ የሚያስቡ ሰዎች ናቸው። ይህ አመለካከት እርምጃዎቻችንን ሊደርሱብን ከሚችሉት ውድቀቶች ጋር አመዛዝነን የመንቀሳቀሳችንን ሁኔታ የሚወስን አመለካከት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን የአንድ ጊዜ ውደቀት ውዳቂነት አይደለም፣ የአንድ ጊዜ አለመሳካት ስኬተ-ቢስነት አይደለም።

✍ **ዶ/ር እዮብ ማሞ**

## ከታላላቅ ሰዎች አንደበት!

⇒ በዝናብ ውስጥ መሄድ እወዳለው ምክንያቱም ሰዎች እኔ ሳለቅስ ሊያዩኝ አይችሉም!  **ቻርሊ ቻፕሊን**

⇒ ምናብ ከእውቀት ይበልጣል፤ እውቀት የተገደበ ነው ነገር ግን ምናብ አለምን ይዞራል!  **አልበርት አንስታይን**

⇒ እኔ በህይወት ካሉት ሰዎች ሁሉ ጠቢብ ነኝ፤ ምክንያቱም አንድ የማውቀው ነገር አለ እሱም ምንም እንደማላውቅ ነው!  **ፕሉቶ**

**በዚህ መጽሔት ላይ እንዲወጣላችሁ የምትፈልጉትን  መረጃዎች፣ አስደናቂ፣ አስቂኝ፣ ወይም አዝናኝ ጽሁፎች ወይም ፎቶግራፎች**